Rushern L. Baker, III
County Executive

# FAQ

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

Prince George's County
DEPARTMENT OF THE ENVIRONMENT
Adam Ortiz | Director

### ለምንድን ነው ካውንቲው በፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ ውስጥ የሚገኙ የምግብ አገልግሎት ምርቶች

### ፖሊስታሪን (polystyrene) (በተለምዶ“ስታይሮፎም” ተብሎ የሚታወቀው) የመሸጥ እና የመጠቀም ማዕቀብ ያደረገው?

ወደ ቆሻሻ መቅበሪያ ውስጥ የሚገባውን የፖሊስታሪን ቆሻሻ መጠን እና ወደ መንገዶቻችን፣ ሰፈራችን እና የውሃ መውረጃዎቻችን የሚገባውንም ቆሻሻ ለመቀነስ፤ ካውንቲው ለአካባቢ-ተስማሚ የሆኑ ከፎም-ነጻ የሆኑ የምግብ ማሸጊያ ምርቶችን መጠቀም እና ሁሉም ሰው “PGC ውስጥ ከፎም-ነጻ” እንዲሆን ይጠይቃል።

ፖሊስታሪን (በተለምዶ ስታይሮፎም ™ ወይም ፎም ተብሎ የሚታወቀው) በአናኮስትያ የውሃ ተፋሰስ ጋር አብሮ በብዛት ይገኛል። ክብደቱ ቀላል በመሆኑ ከጎዳናዎች እና ከእግረኛ መንገዶች በቀላሉ በነፋስ እና በዝናብ አማካኝነት በቀጥታ ወደ ጎርፍ መውረጃ በመግባት ወደ ወንዞችና ጅረቶች ይገባል። በውሃ ውስጥ ፎም ወደ ትናንሽ ቁርጥራጭ ይቆራረጥ እና የካውንቲውን የውሃ ክፍል ይበክላል፤ በመቀጠልም የዱር እንስሳት በስህተት ሲመገቡት በሰውነታቸው ውስጥ ተጠራቅሞ በምግብ ሰንሰለት ውስጥ ጎጂ መርዝን ይፈጥራል። ለዓይን የሚያስጠላ የፎም ቆሻሻ ብቻ ሳይሆን በካውንቲው በሚገኙ የውሃ አካላት፣ የዱር እንስሳት እና ዜጎች ጤንነት ላይ ጎጂ ውጤት አለው።

በተጨማሪም፤ ፎም አብዛኛውን ጊዜ ሪሳይክል አይደረግም።




### “PGCን ከፎም (FOAM)ነጻ የማድረግ” ጥረት የጀመረው መቼ ነው?

ጁላይ 1/ 2016

### የትኞቹ ንግዶች ላይ ነው ተጽዕኖ የሚያሳድረው?
(የሚከተሉትን ጨምሮ ነገር ግን በነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም)

- ሙሉ እና የተወሰነ-አገልግሎት ምግብ ቤቶች
- የፋስት ፉድ ምግብ ቤቶች
- ካፌዎች እና በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ምግቦች መሸጫዎች
- ካፍቴሪያዎች
- የቡና መሸጫ ሱቆች
- የቅናሽ መደብሮች
- የዶላር መደብሮች
- ሱፐርማርኬቶች እና የግሮሰሪ ሱቆች
- የምግብ መሸጫ ሰረገሎች ወይም ትራኮች
- የማሸጊያ እና የመልእክት መላኪያ ሱቆች
- ከተጠቀሙ በኋላ የሚጣሉ ሳህኖች፣ የማጠራቀሚያ መያዣዎች፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶች እና የፖሊስታሪን

### የፎም ምርቶች ላይ ማዕቀብ የማድረግ ስልጣን ያለው የፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ ብቻ ነው?

አይደለም። ዋሽንግተን ዲሲ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ እና በሜሪላንድ ውስጥ የታኮማ ፓርክ ከተማም እንዲሁ የፎም ቆሻሻ ለመቀነስ “ከፎም ነጻ የማድረግ” ሕግ አሳልፈዋል።

### ለአንድ-ጊዜ የሚያገለግሉ አንዳንድ የፎም የምግብ አገልግሎት ምርቶች ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?



- ኩባያዎች
- ሳህኖች
- ጎድጓዳ ሳህኖች
- ይዞ የመሄጃ መያዣዎች
- ትሪዎች
- የማሸጊያ ፎሞች/ፒነቶች

### ተቀባይነት ያላቸው አማራጭ ምርቶች ምንድን ናቸው እንዲሁም ከየትስ መግዛት ይቻላል?



ሪሳክል ሊሆኑ ከሚችሉ ወይም በቀላሉ ከሚበሰብሱ እንደ ትሪዎች፣ ሳህኖች፣ ጎድጓዳ ሳህኖች፣ ኩባያዎች፣ በወረቀት የተሰሩ ምርቶች እና ሌሎች ሪሳይክል በሆነ ማቴሪያል የተሰሩ ለአካባቢ-ተስማሚ የሆኑ አማራጮች ማግኘት ይቻላል። ከፎም-ነጻ የሆኑ የምግብ አገልግሎት ምርቶች ከተለያዩ አቅራቢዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት ይቻላል። አማራጭ ወይም ተቀባይነት ያላቸው ምርቶችን የሚያቀርቡ የአቅራቢዎች ዝርዝር environment.mypgc.us/foamfree ላይ ማግኘት ይቻላል።

# PGCን ከፎም ነጻ ማድረግ

በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የትኞቹ የፎም ምርቶች ናቸው ነጻ የተደረጉት?

- ከፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ ውጪ የተሞሉ እና የታሸጉ የምግብ እና የመጠጦች ማሸጊያ ፎም
- ከአካባቢ ውጭ ለሚውል ፍጆታ ለጥሬ፣ ላልበሰለ ወይም ለታረደ ሥጋ፤ ዓሣ፣ የዶሮ ሥጋ ወይም የባሕር ውስጥ ምግብ ማሸጊያ ፎም

## አንድ ምርት በፎም የተሰራ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለሁ?

በምርቱ መግለጫ ውስጥ የሚከተሉት ቃላት ያሉባቸውን ማናቸውንም ነገሮች አይግዙ፡-

- የሚለጠጥ  ፖሊስታሪን (polystyrene)
- ፖሊስታሪን (polystyrene)
- ፎም (Foam)
- #6 EPS

## የተከማቸ ወይም ለሽያጭ የተቀመጠ ትርፍ የፎም እሽጌን ምን አደርግዋለሁ?

ለበለጠ መረጃ እባክዎን 3-1-1 ላይ CountyClick ያነጋግሩ።

## ይህ ሕግ እንዴት ነው ተፈጻሚ የሚሆነው?

ለመጀመሪያው ጥሰት ማስጠንቀቂያዎች ይሰጣሉ። ለሁለተኛው ጥሰት የ$250 መቀጮ እንዲሁም በ12 ወር ውስጥ ለሚደረግ ሦስተኛ ጥሰት የ$1000 መቀጮ ይሰጣል። በየአንዳንዱ ቀን ጥሰት ከተከሰተ የተለየ ጥፋት ተደርጎ ይቆጠራል።

## እንዴት ነው ንግድ ቤቶች ማስታወቂያ የሚደርሳቸው?

“PGCን ከፎም (FOAM)ነጻ የማድረግ”ን በተመለከተ ፖስትካርዶች ከዝርዝር መረጃ ጋር በካውንቲው ለሚገኙ ንግድ ቤቶች በሙሉ በፖስታ ተልኳል። የመረጃ ማቴሪያሎችም በኦንላይን environment.mypgc.us/foamfree ላይ ማግኘት ይቻላል።

## የፎም ምርቶችን መጠቀም የቀጠሉ የንግድ ቤቶች ወይም ድርጅቶችን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?

እባክዎን countyclick.princegeorgescountymd.gov በመጎብኘት ጥቆማዎችን ለ countyclick ሪፖርት ያደርጉ ወይም 3-1-1 ይደውሉ። ሁሉም ጥቆማዎች በሚስጥር ሊያዙ ይችላሉ።  የ DoE ተቆጣጣሪው የተቋቋመበት ምርመራ በመምራት በማድረግ ሪፖርቱ ጋር ክትትል ያደርጋል

## ለበለጠ መረጃ ማንን ማነጋገር እችላለሁ?

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር foamfreePGC@co.pg.md.us ፤ Angela Angel ን ያነጋግሩ።